የሰበር መ/ቁ. 32143

ጥቅምት 18 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- መሐመድ እስማኤል ተርቢ

**ተጠሪ**፡- መሐመድ አሕመድ ኑር

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ በአፈፃፀም ደረጃ ያለውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ገንዘብ ይከፍለው ዘንድ ያስወሰነ የፍርድ ባለመብት ነው፡፡ እንደውሣኔው ለማስፈፀምም የአፈፃፀም መዝገብ አስከፍቶ ገንዘቡን ገቢ ለማድረግ ሲባል የሐራጅ ማስታወቂያ ወጥቶበት ገዢ አልተገኘለትም የተባለውን የተጠሪን ቤት እንዲረከብ አሣዝዞአል፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ተጠሪ በዚህ ላይ ለበላይ ፍ/ቤቶች ይግባኝ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም ክርክሩ ተቀባይነት ባለማግኘቱ አፈፃፀሙን የጀመረው በሶማሌ ብ/ክ/መ/የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የተጠሪን ቤት አመልካች እንዲረከብ በድጋሚ አዟል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የክልሉ ጠቅላይ /ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ተጠሪ እና ሌሎች ስድስት ሰዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት መቃወሚያ አቅርበውልኛል በማለት የቀድሞ ውሣኔውን /የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን የአፈፃፀም ውሣኔ በማጽናት ሰጥቶት የነበረውን/ በመለወጥ አመልካች ቤቱን ሊረከብ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሐምሌ 24 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ባለመቅረቡ ክርክሩ እሱ በሌለበት ነው የተሰማው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የስር ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት የቀረበለትን መቃወሚያ ያስተናገደበትን እና የቀድሞውን ውሣኔ የሻረበትን አግባብ ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ለስር ፍ/ቤቶች ከቀረበው ክርክር፣ ከአመልካች አቤቱታ እና አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እንዲሁም ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምናየው ተጠሪ ለአመልካች የሚከፍለው ገንዘብ አለ ተብሎ የተወሰነበት ሰው ነው፡፡ ይህን ገንዘብ ለማስከፈል ሲባልም ንብረቱ ነው በተባለው ቤት ላይ የአፈፃፀም ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡ ይህን የአፈፃፀም ትእዛዝ በመቃወም ለሶማሌ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የተለየ ትእዛዝ /ውሣኔ/ አስጥቶ የነበረ ቢሆንም አመልካች ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ባቀረበው አቤቱታ መነሻነት ክርክር ከተደረገ በኂላ አፈፃፀሙ የከፍተኛው ፍ/ቤት በሰጠው ትእዛዝ መሠረት እንዲቀጥል ተወስኗል፡፡ ይህ ሁሉ ከሆነ በኂላ ነው ተጠሪ ተቀዋሚ በመሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት ለሰበር ችሎቱ አቤቱታ ያቀረበው፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት አቤቱታ /መቃወሚያ/ የሚቀርበው ቀደም ሲል የተሰጠን ውሣኔ ለመቃወም ነው፡፡ መቃወሚያውን ማቅረብ የሚችሉትም ቀደም ሲል በተደረገው ክርክር ተካፋይ ያልነበሩት ወገኖች ናቸው፡፡ ተጠሪ ቀደም ሲል በተደረገው የአፈፃፀም ክርክር ተካፋይ የነበረ እና የተወሰነበት ሰው ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ በኂላ ተቃዋሚ ሆኖ የሚቀርብበት አግባብ የለም፡፡ ሌሎቹ ሰዎችም ተቃዋሚ ሆነው የቀረቡት የአፈፃፀም ትእዛዝ የተሰጠበት ንብረት

የተጠሪ ብቻ ሣይሆን የውርስ ሃብት ነው በሚል እንደሆነ ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ በእርግጥ እነሱ እንደሚሉት ንብረቱ የእነሱም የውርስ ሃብት ከሆነ የአፈፃፀም መዝገቡ ለተከፈተበት የከፍተኛው ፍ/ቤት በጊዜው ሊያቀርቡ ይችሉ /ይገባቸው/ ነበር፡፡ በአፈፃፀም በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት ላይ መብት አለን ባዮች አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 418 መሠረት ሆኖ ማቅረብ ያለባቸውም ሣይዘገዩ እንደሆነ በዚሁ ቁ. 418/1/ ተመልክቶአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ሰዎቹ አቤቱታቸውን ያቀረቡት አፈፃፀሙን ለያዘው ለከፍተኛው ፍ/ቤት ሣይሆን የመጨረሻ ውሣኔ ለሰጠው ለሰበር ችሎቱ ነው፡፡ ከዚህም በላይ በንብረቱ ላይ ከተጠሪ ጋር የጋራ መብት አለን ባዮች ሆነው ሣለ ተጠሪ በከፍተኛው ፍ/ቤት ከአንዴም ሁለቴ በጠ/ፍ/ቤት እና በሰበር ችሎትም እንደዚሁ በክርክር በቆየበት ጊዜ ተቃዋሚ ሆነው አልቀረቡም፡፡ ይህም ሲታይ ለረዥም ጊዜ በንብረቱ ላይ መብት አለን በማለት መቃወሚያ ሣያቀርቡ ዝም ብለው መቆየታቸውን ያስገነዝባል፡፡ በዚህ ሁኔታ የቀረበን አቤቱታ ፍ/ቤቱ እንደማይመረምረው በተጠቀሰው ድንጋጌ ተመልክቶአል፡፡ በመሆኑም አቤቱታው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 418 መሠረት እንደቀረበ ይቆጠር እንኳን ቢባል ያለበቂ ምክንያት በመዘግየቱ የተነሣ የሚመረመርበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ሰበር ችሎቱ የሰጠው ውሣኔም ከዚህ አንፃር ሲታይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ሊባል የሚችል ነው፡፡

## ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በሶማሌ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. ኤም.ጂ. 12/99 ሰኔ 20 ቀን 99 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 418/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ያለው የአፈፃፀም ጉዳይ የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 15/95 ሰኔ 26 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ መሠረት ይቀጥል ብለናል፡፡
   መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ